# አይ ላይክ ዘ ዊንድ (I Like the Wind)




## የ አር አይ ኤፍ (RIF) መምሪያ ለቤተሰቦች

ይዘቶች (Themes)፤ ጓደኝነት፤ የአካባቢ ጥበቃ (Environmentalism)፤ የአየር ሁኔታ

የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፤ ጓደኛሞች ነፋሻማ በሆነ ቀን እየተደሰቱ በነፋሻ ቀን ውስጥ ሊከሰቱ ስለሚችሉ አስደሳች ነገሮች ሁሉ ያካፍላሉ። በመፅሃፉ መጨረሻ ላይ ስለ ንፋስ እና ሰዎችን እና አካባቢን እንዴት እንደሚጠቅም አንዳንድ እውነታዎች አሉ።

ደራሲ፤
ሳራ ኔልሰን (Sarah Nelson)

ሰዓሊ (Illustrator)፤
ራቼል ኦልድፊልድ
(Rachel Oldfield)

## የማንበብ ጊዜ!



ከንባብ በፊት፤ ለልጅዎ እንዲህ ይበሉት፤ "የዚህ ታሪክ ርዕስ አይ ላይክ ዘ ዊንድ የሚል ነው።ነፋሱን ትወዳለህ? ለምን ትወደዋለህ ወይም ለምን አትወደውም? እስቲ እነዚህ ልጆች ነፋሱን እንደሚወዱት እንይ።"

በንባብ ጊዜ፤ በሚያነቡበት ጊዜ፣ ልጅዎ በታሪኩ ውስጥ ያሉ ልጆች በነፋስ የሚወዷቸውን ልዩ ልዩ ነገሮች ሁሉ እንዲጠቁሙ ያድርጉ። እነዚህ ልጅዎ ማድረግ የሚወዳቸው ነገሮች መሆናቸውን ይጠይቁ። በነፋስ ውስጥ ምን ሌሎች ነገሮች አስደሳች ሊሆኑ ይችላሉ? እንዲሁም በመጽሃፉ ገጽ ላይ ነፋሻማ መሆኑን እንዴት እንደሚነግሩ ይጠይቋቸው። በሥዕሉ ላይ ነፋሻማ መሆኑን እንዲያውቁ የሚያስችላቸው ምን ይታያቸዋል? በአቅራቢያቸው በነፋስ ቀናት ውስጥ ምን ያዩታል?

ከንባብ በኋላ፤ ጥያቄዎች ይጠይቁ፤

- ታሪኩ ውስጥ ነፋሱ ምን ይሰራል?
- እምንኖርበት ቦታ ነፋሱ ምን ሲሰራ ተመለከትክ?
- በነፋሳማ ቀናት ምን መስራት ትወዳለህ?

## ውይይት ጀማሪዎች (CONVERSATION STARTERS)

ስለ ጽሁፉ ማሰብ፤ ልጆች መጽሃፍት ሲያነቡ እና በመጽሃፍት ሲደሰቱ፤ ፅሁፍ እንዴት እንደሚፃፍ እና የታሪኩን ይዘት እና ትርጉም እንዴት እንደሚጋራ ማወቅ ይጀምራሉ። ይህ መጽሐፍ ጓደኛሞች በነፋሻማ ቀን ስለሚዝናኑበት እውነተኛ ልብ ወለድ ታሪክ ያካፍላል። በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ስለ ንፋስ እውነታዎችን የሚያካፍል መረጃዊ ጽሑፍ ያካትታል። መጽሐፉን ሲያነቡ በእነዚህ ሁለት የጽሑፍ ዓይነቶች መካከል ያለውን ልዩነት ይግለጹ። "የመጽሐፉ የመጀመሪያ ክፍል ልጆች በነፋስ ስለሚዝናኑበት ታሪክ የተሰራ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል በእውነተኛ ህይወት ውስጥ ስለ ንፋስ የበለጠ እንድንማር ይረዳናል። ይህ መጽሐፍ አስደሳች ታሪክ እና እውነተኛ ክስተቶች አሉት።

## ተዛማጅ ተግባራት

**ነፋሱን አያለሁ - የጣት ጨዋታ**

ይህን አስደሳች የጣት ጨዋታ ከልጅዎ ጋር በቤትዎ ውስጥ ይሞክሩት!

ቅጠሎቹ ሲጨፍሮ ነፋሱን አያለሁ (አጆችዎን ያስጨፍሩ)
ልብሱ ሲወዛወዝ ንፋሱን አያለሁ "ሃይ (Hi)!" (እጆችዎን ያወዛውዙ)
ዛፎቹ ዝቅ ብለው ሲታጠፉ ንፋሱን አያለሁ (እጆችዎን ከላይ ወደታች ይጠፉ)
ባንዲራዎቹ በአየር ሲሞሉ ነፋሱን አያለሁ(እጆችዎን ወደኋላ እና ወደፊት ያወዛውዙ)

ካይትስ (kites) ከፍ ብሎ ሲበር ንፋሱን አያለሁ (እጆችዎን የቻሉትን ያህል ወደላይ ያንሱ)

ደመናው ሲንሳፈፍ ንፋሱን አያለሁ (እጆችዎን ቀስ ብለው ልክ እንደደመና ያንሳፉ)
ሰጉሬ ሲወዛወዝ ንፋሱን አያለሁ(ሰጉርዎን በእጅዎ ወደላይ ያንሱ፤ ወይም ዘጉርዎን በጭንቅላትዎ ያወዛውዙ)
ነፋሱን ሁሉምጋ በሚባል ሁኔታ አያለሁ! (በአካባቢው ሁሉ በእጆችዎ እንቅስቃሴ ያሳዩ)

ነፋሻማ በሆነ ቀን ወደ ውጭ ይሞክሩት እና በዙሪያዎ ያሉትን ማንኛውንም ድርጊቶች ካስተዋሉ ይመልከቱ!

## ተጨማሪ ሪሶርሶች (RESOURCES)



**ተከታታይ የሆኑ ሌሎች የአየር ሁኔታ መጻህፍት**

- አይ ላይክ ዘ ሰን (I Like the Sun) (2021)
- አይ ላይክ ዘ ሬይን (I Like the Rain) (2021)
- አይ ላይክ ዘ ስኖው (I Like the Snow) (2021)

©2024 Reading Is Fundamental

Reading Is Fundamental | Read for Success Early Childhood